በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል 1

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**መጋቢት ፬ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል 1</u>

## ***<u>እምነት ከስሜቶቻችን በላይ ነው</u>***

- እምነት ውስጉን ከሆኑት ስሜቶቻችን የላቀ ኃይል ነው፡፡
- ስሜቶቻችን አካላዊና ቁሳዊ የሆኑ ነገሮችን ቢመርምሩ እንጂ ከእነዚህ ውጪ የሆኑትን አይችሉም፡፡
- ስሜቶቻችን መፈተሽ የማይችሉትን ዝርዝር ነገሮች ለመመርመር እንዲያስችሉን የተለያዩ የመመርመሪያ ቁሳቁሶችን እንጠቀማለን፡፡ ታዲያ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለነገረን ‹‹ለማይታዩ ነገሮችስ›› ወይም አካላዊ ላልሆኑ ነገሮችስ ምን ያህል ያስፈልገን ይሆን?
- ‹‹በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና ›› ***<u>ካል ቆሮ 5፡7፡፡</u>*** እንደተባለው እምነት በሰው የሥጋ ዓይን የሚታየው አይደለም፡፡
- ነፍሳችን በስሜቶቻችን አትታይም፤ ስሜቶቻችንም የነፍስን መኖር አለመረዳታቸው ነፍስን የለችም አያሰኛትም፡፡ ስሜቶች በልክም በደረጃም ወደ ነፍስ ምርምር ለመድረስ ውሱን ናቸውና፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል 1

## ***እምነት ከማስተዋላችን (ችሎታችን) በላይ ነው***

- ማስተዋላችን (ችሎታችን) ወደ መንገዳችን መጀመሪያ ቢያደርሰንም እስከ መንገዱ መጨረሻ የሚያደርሰን ግን እምነት ነው፡፡
- እምነት ከማስተዋላችን (ችሎታችን) ጋር ጠብ ባይኖረውም ነገር ግን አእምሮአችን ሊደርስ ወደ ማይችልበት ከፍ ያለ ደረጃ የሚያደርሰን ነው፡፡
- አእምሮ የማይደርስበትን ነገር ሊቆጣጠር የማይቻለው ነው፡፡ እግዚአብሔርን መጠን መመርመር የሌለበት አኃዜ ኩሉ የምንለው የማይወሰን ስለሆነ ነው፡፡
- የሰው አእምሮ ግን ውሱን ነው፤ መረዳትም የምንችለው የተወሰኑ ነገሮችን ብቻ ነው፡፡
- አእምሮ እግዚአብሔር ወደ ማወቅ የተወሰነ ባሕርይውንም ወደ መረዳት ሊያደርሰን ይችላል፡፡ ነገር ግን ‹‹ መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው። ›› ***ቀዳ ቆሮ 2፡10፡፡*** እንዳለ በእምነት ጥልቅ የሆነውን እንረዳለን፡፡
- አእምሮ ሁሉን መቅሰም ባይችልም ሊቀበላቸው ይገባል፡፡ በተፈጥሮም አእምሮ ያልተረዳውን ሁሉ ለመቀበል እምቢተኝነት የለበትም፡፡ በዓለማችን የፈጠራው ባለሞያዎች ብቻ የሚያውቋቸውን ነገሮች መደዴ የሆነው የእኛ አእምሮ ነገሮች እንዴት እንደሚሠሩ ባያውቅም ይቀበላቸዋል፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል 1</u>

## *<u>እምነት ከማስተዋላችን (ችሎታችን) በላይ ነው</u>*

- አእምሮ ሞትን ባይቀምስና ባይረዳውም ሞትን ይቀበላላል ስለ ሞትም ይናገራል፡፡
- አእምሮ በዚህ ዓለም ያሉ በርካታ ነገሮችን ሳይረዳ የሚቀበላቸው ከሆነ ከዚህ ዓለም ያልሆነውን ነገር እንዳይቀበል የሚከለክለው ነገር አይኖርም፡፡
- አእምሮ እንዴት ተአምራት እንደሚሠሩ ባያውቅም ይቀበላቸዋል በተአምራቱም ደስ ይለዋል፡፡ ተአምር ተአምር የተባለው አእምሮ አውቆት ሊያስረዳው ስለማይችል ነው፡፡
- አእምሮ ተአምርን በማይወሰን ከአእምሮ በላይ በሆነ ሊረዳው በማይችለው ኃይል የተነሳ በእምነት ይቀበለዋል፡፡ ይህም ኃይል ሁሉን ቻይ የሆነ የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡
- ውሱንነቱንም ከማወቅ ጋር አእምሮን እናከብራለን ፡፡ ከአእምሮ (ከመረዳት) በላይ የሆኑ ነገሮች እንዳሉ ዘንግቶ ሁሉን ልወቅ ባይ የሆነ ትምክህተኛ አእምሮንም አንቀበለውም፡፡
- አእምሮ ውሱንነቱን ለማወቅ ትሁት መሆን ይገባዋል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፥ እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ።›› ***<u>ሮሜ 12፡3፡፡</u>*** እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ፡፡
- አእምሮ ከራሱ መረዳት በላይ የሆኑ ነገሮችን ለእምነት አሳልፎ መስጠት አለበት፡፡
- አእምሮ የማይረዳውን ሁሉ ከንቱ የሚያደርገው ከሆነ ራሱን በማጥፋት ብሎም የእምነትን ቅመም በማጣት በጠባብነት የመረዳት አዙሪት ውስጥ ራሱን ይጥላል፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል 1</u>

## ***<u>እምነት ከማስተዋላችን (ችሎታችን) በላይ ነው</u>***

- አማንያን ልባሞች ናቸው፤ አእምሮአቸውን በማክበር ለመንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ይጠቀሙበታልና፡፡
- ከአማንያንም መካከል በራሳቸው አእምሮ መረዳት የማይደገፉ አእምሮአችን ሁሉን መረዳት ይችላል ብለው የማይመኩ ፈላስፎችና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ሰዎችም አሉ፡፡ እነዚህም ሰዎች በአትሕቶ ርእስ ስለ እግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ መረዳት እንደማይችሉ  አእምሮአቸውም ውሱን እንደሆነ ዘወትር ይናዘዛሉ፡፡ በእምነት ልባቸውና አእምሮአቸውም ከአእምሮአቸው በላይ የሆነውን ሁሉ አምኖ ይቀበላል፡፡
- የዋሕና ትሑት አእምሮ እምነትንና ተአምራትን አምኖ ይቀበላል፡፡ ትሑት ስንልም በራሱ ሐሳብ የማይደገፍ፣ ያልተረዳውንም ሁሉ የሚያጠፋ፣ ከራሱ የሚያርቀውም ያልሆነ፣ በውሱንነቱ ላይ ሁሉን በመከመር ነገሮችን ውስብስብ የማያደርገው አእምሮ ማለታችን ነው፡፡
- እምነት የምንጸልየው ጸሎት ብቻ ሳይሆን የምንኖረውም ሕይወት ነው፡፡ የእምነትን ሕይወት የምንኖር ከሆንን የእምነት ፍሬዎች በተግባራዊ ሕይወታችን ግልጥ ይሆናሉ፡፡
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ***<u>2ኛ ቆሮ 13፡5</u>*** ‹‹ በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን? ›› እንደጻፈልን በአማንያን ሕይወት በሚታዩት የበዙ በሆኑት መንፈሳዊ እሴቶች ሚዛን እያንዳንዳችን እምነታችንን እንመርምር፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል 1

## ***የማይታየውን በጽንዓት ማመን***

- ሐዋርያው ስለ እምነት ‹‹እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።›› ***ዕብ 11፡1*** ብሎናል፡፡
- ጽንዓት ያለጥርጥር የሆነ እምነት (ማመን) ነው፡፡ ይህም መደዳ ሐሳብ፣ አመለካከትን ወይም ከማንበብ ወይም ከመስማት የተገኘውን እውቀት ማመን ሳይሆን የማይታዩ ነገሮች አሉ ብሎ ማመን ነው፡፡ የሚያምኑና የማያምኑ (የሳይንስ ሰዎች) የሚለያዩት በዚህ ነው፡፡
- የማይታዩ ነገሮች የምርምር ሰዎች የሥራ መስኮች አይደሉም:: እነዚህ ሰዎች ስለ አንድ ነገር እርግጠኞች ካልሆኑ በጥልቀት በተለያዩ የምርምር መሣሪያዎቻቸው ምርምር ያደርጋሉ፡፡ ይህም በቁሳዊ ነገሮች በሚያምኑ ሰዎች ሕይወትም የሚታይ ነው፡፡
- የሚያምኑ (አማንያን) ግን ‹‹ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው።›› ***ዮሐ 20፡29*** እንዳለው ናቸው እንጂ እንደዚህ አይደሉም፡፡
- የሚያምኑ (አማንያን) እግዚአብሔር ፍጥረትን ከምንም እንደፈጠረ አምነው ይቀበላሉ፡፡
- የሳይንስ ተመራማሪዎች ግን ይህን ይክዳሉ፤ ብሎም በአምስቱ እንጀራ አምስት ሺህ ሰዎች (ሴቶችንና ሕጻናትን ሳይጨምር) መግቦ አሥራ ሁለት መሶብ እንጀራ ማትረፉን አይቀበሉትም አማንያን ግን እነዚህን ሁሉ አምነው ይቀበላሉ፡፡ ***ማቴ 14፡፡***

# የእምነት ሕይወት - ክፍል 1

## ***የማይታየውን በጽንዓት ማመን***

- የሚያምኑ (አማንያን) አስቀድመው እግዚአብሔር ኃያል እንደሆነ ያምናሉ ከምርምር ሰዎች ጥርጣሬና ከማያምኑ ሰዎች ግኝቶች ራሳቸውን ያርቃሉ፡፡
- የሚያምኑ (አማንያን) የማይታየውን መቀበል ብቻ ሳይሆን ሐዋርያው ‹‹የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው፡፡›› ***ካል ቆሮ 4፡18*** እንደጻፈው አእምሮአቸውንና መነካታቸውንም በማይታየው ላይ ያደርጋሉ፡፡
- የማይታየውን እንዴት አየዋለሁ? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን የሚታየው በእምነት ነው እንላችኋለን፡፡ የማይታዩትስ እነዚህ ነገሮች ምንድር ናቸው? ከማይታዩትም የመጀመሪያው እግዚአብሔር፣ ባሕርይው፣ *ሥራውና* የእርሱ የሆኑ ነገሮች ናቸው፡፡

## *1. **የእግዚአብሔር ባሕርይ እና ሥራ***

- ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም›› ***ዮሐ 1፡18*** እንደጻፈው እግዚአብሔር በመለኮቱ አይታይም፡፡ በርግጥ መለኮትን ማን ሊያይ ይችላል? ማንም! ነገር ግን በፍጹም ልባችንና ሐሳባችን በርሱ እናምናለን፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል 1</u>

## *<u>የማይታየውን በጽንዓት ማመን</u>*

### *1. <u>የእግዚአብሔር ባሕርይ እና ሥራ</u>*

- ነገር ግን በተለማመደው መንፈሳዊ ስሜታችን እናየዋለን ልንል እንችል ይሆናል እንጂ እግዚአብሔርን በአካላዊ ስሜቶቻችን አናየውም፡፡ ‹‹ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።›› ***<u>ዕብ 5:14፡፡</u>***
- አካላዊ ያልሆኑ ስሜቶቻችን የማይታየውን እንዲያዩ ይለማመዳሉ፡፡ ይህንም የሚያስረዱን የሚከተሉትን ምሳሌዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን፡፡
  - ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ በቀኜ ነውና አልታወክም።›› *መዝ* 15:8፡፡ ሲል እግዚአብሔርን በፊቱና በቀኙ ዘወትር ሊያየው የተቻለው እንዴት ነው? ያለምንም ጥርጥር ያየው በእምነት ዓይን ነው፡፡ ልበ አምላክ የማይታየውን ዘወትር በተመስጦ በሆነ አእምሮና መንፈሳዊ ስሜት ያየው ነበር፡፡
  - በተመሳሳይ ትርጉምም ነቢዩ ኤልያስ ‹‹ኤልያስም። በፊቱ የቆምሁት የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔርን! እኔ ዛሬ ለእርሱ እገለጣለሁ አለ።›› ***<u>ቀዳ ነገ 18:15</u>*** ብሏል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት እንደቆመ እንዴት ሊሰማው እግዚአብሔርንስ በፊቱ እንዴት ሊያየው ቻለ? ይህ የሆነው በእምነት እንጂ የአማንያንን ልቦና ሊያነቃቃ በማይችላው በአካላዊ ስሜት አይደለም፡፡ የማይታየውን የሚያየው እምነት ነውና፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል 1

## *የማይታየውን በጽንዓት ማመን*

### 1. *የእግዚአብሔር ባሕርይ እና ሥራ*

- በእምነት ከሆንን በሙሉ ልብ እግዚአብሔር ሁልጊዜ በፊታችን እንደሆነ ይሰማናል፤ በዚህም እምነት እንራመዳለን፤ እግዚአብሔርም ይሰማናል ያየናልም።
- በእምነት የምንኖር ከሆንን ‹‹..በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።›› ***ማቴ 18፡20***፣ ‹‹… እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።›› ***ማቴ 28፡20*** ባለው ቃል ኪዳኑ እግዚአብሔር በሕዘቦቹ መካከል እንደሚኖር እርግጠኞች እንሆናለን።
- እርሱ እግዚአብሔርን በሥጋ ዓይናችን አይተነው ሳይሆን በመካከላችን እንዳለ ፈጽመን እናምናለን። ለማመን የግድ በሥጋ ዓይናችን ካላየን አንልም።። ሳናይ እናምናለን የማይታየውንም ለይተን እናውቀዋለን እናየዋለንም።
- መንፈሳዊ ሕይወትስ ምንድር ነው? በሥጋ ከሚሰማንና ከሚታየን ወጥተን ወደማይታየን መሸጋገር አይደለምን?
- በማናየው በጽንዓት አምነን እንኖራለን እርሱ በፊታች ነውና። ይህም የሚያምኑና የማያምኑ የሚለያዩበት መንገድ ነው።

# የእምነት ሕይወት - ክፍል 1

## *የማይታየውን በጽንዓት ማመን*

### *1. የእግዚአብሔር ባሕርይ እና ሥራ*

- የማያምን ሰው ሁሉን ነገር በዓይኑ ማየት ይፈልጋል፤ ካላየ ግን አያምንም፡፡
- የሚያምን ሰው ግን ዓይኑ፣ ስሜቶቹ ወይም ውጫዊ ክስተቶች እምነቱን ቅርጽ እንዲያስይዙት ዕድል አይሰጥም፤ ይልቁኑ ልቦናው የማይታይ ነገር እንዳለ በማመን ይጸናል እንጂ፡፡
- በአንድ ወቅት ጌታችን እግዚአብሔር የነገረውን ለማመን የተሳነው ደቀ መዝሙሩን ቶማስን ‹‹ከዚያም በኋላ ቶማስን። ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። … ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።›› ***ዮሐ 20፡27፤29፡፡*** በማለት ገስጾታል፡፡
- አስቀድመን እንደገለጽነው በእግዚአብሔር ማመን በማናየው ነገር ጸንተን ከማመን መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህም በእግዚአብሔር መኖር ብቻ  ሳይሆን በባሕርዩና በሥራው ማመን ነው
- ‹‹በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል አለ።›› ***ሉቃ 18፡27፡፡*** እንዳለ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑንና ለእኛና ለፍጥረቱ ለሰዎች ስላለውም ልዩ የሆነ ፍቅር እናምናለን፡፡
- እነዚህን ሁሉ በዓይናችን ላናያቸው እንችላለን ነገር ግን እናምንባቸዋለን፡፡ እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ እንደሚጠብቅ ውበትዋንም እንደሚጠብቅ እናምናለን፡፡ እያንዳንዱንም ሰው እንደሚጠብቅም እናምናለን፡፡ ስናምንም ሥራውን ወይም ውጤቱን ልናይ ወይም ምንም ነገር ላናይ እንችላለን፤ ባናየውም እንኳ እናምነዋለን፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል 1

## ***የማይታየውን በጽንዓት ማመን***

## *2. የእግዚአብሔር ጊዜ*

- ‹‹እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፥ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት፥ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ።›› ***ዕብ 11:13*** የተባሉት እነዚህ የእምነት ሰዎች ተብለዋል፡፡ እነርሱም በእምነት ቃል የተገባላቸውን በተስፋ ጠበቁ፣ እግዚአብሔር የነገራቸውንም አመኑ፡፡
- ቃልኪዳኑም ‹‹ነገር ግን። ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንድተጻፈ፥ እንዲህ እንናገራለን።›› ***ቀዳ ቆሮ 2:9፡፡*** የተባለው ነው፡፡
- የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ የማይታይ ነገር ነው፡፡
- ኖኅ እግዚአብሔር ዓለምን በንፍር ውሃ አጠፋዋለሁ ብሎ ሲነግረው የንፍር ውሃ ምን እንደሆነ ባያውቀውም አመነ፡፡
- በኖኅም ሆነ ከርሱ በፊት የንፍር ውሃ (ታላቅ ጎርፍ) በዓለም ታይቶ ባይታወቅም እስካሁን ያልሆነ ይሆናል ይደረጋል ብሎ አመነ፡፡ የሌሎችን ነቀፋና ትችት ችሎ መርከቢቱን በመሥራቱ በረታ፤ ይህም እምነቱ ለዘመናት የጠበቀው እምነት ነበር፡፡
- ኖኅ ለእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ትኩረት ስለሰጠ የእምነት ሰው ተባለ፡፡ የንፍር ውሃን ከመምጣቱ በፊት በእምነት ለማየት ተችሎታልና፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል 1</u>

## ***<u>የማይታየውን በጽንዓት ማመን</u>***

### *2. <u>የእግዚአብሔር ጊዜ</u>*

- በእምነት ወደ መርከቢቱ እርሱ ሚስቱ፣ ልጆቹና የልጆቹ ሚስቶች ገቡ። ቅዱስ ጳውሎስም ‹‹ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተ ሰዎቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ፥ በዚህም ዓለምን ኰነነ፥ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።›› ***<u>ዕብ 11፡7</u>*** ብሎ ያስተምረናል።
- የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ያልሰሙና በእግዚአብሔር እውነት ያላመኑት (እምነትም ያልነበራቸው) በንፍር ውሃው ተቀቅለው ጠፍተዋል።
- ሎጥና የሰዶም ከተማም የሚሆነው ከመሆኑ በፊት ማስጠንቀቂያው ተነግሮአቸዋል። በኖኅ ዘመን የሆነው የንፍር ውሃ የመጀመሪያ እንደሆነው ሁሉ ከሰማይ እሳት ሲዘንብም ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር።
- የሰዶምም ሰዎች እንደ ኖኅ ዘመን ሰዎች እግዚአብሔርን ባለማመና የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ባለመቀበል ጠፍተዋል።
- ዛሬም በዘመናችን ፍርድንና ዘላለማዊ ሕይወትንም አስመልክቶ የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ በፊታችን ቢሆንም ብዙዎች አሁንም እግዚአብሔር ያላስጠነቀቃቸው ይመስል በክፋትና በኃጢአት ተዘፍቀዋል።
- በልባቸው እግዚአብሔርንም ሆነ ዘካለማዊ ፍርድን መፍራት የለም።
- የተማርነው ስለእግዚአብሔር፣ ስለ ባሕርዩ ስለ ሥራው፣ ስለ ቃልኪዳኑና ስለማስጠንቀቂያው ነው። በዚህ ርዕስ ሥር ሌሎች ነጥቦችን መጨመር ይኖርብናል… እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሳምንት እንቀጥላለን።

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
[kesisolomon4@gmail.com](mailto:kesisolomon4@gmail.com)

To get all the lessons, surf :
[www.zeorthodox.org](http://www.zeorthodox.org)